# የጾም ጸሎት- የቅድስና መነቃቃት ቅድመ ሁኔታዎች

## የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ ኢዮ 2፡12-17

ይህ ስብከት የሚያሳየው የቅድስና መነቃቃት/ተሃድሶ የሚከሰተው የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሚያደርገው እውነተኛ የጾም ጸሎት እግዚአብሔር በሚሰጠው ምላሽ መሆኑን ያሳያል። ይህም በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ያለንን የናዝሪን ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን በጾም ጸሎት መትጋታችን ያለውን ጠቀሜታ ያሳያል።

ማስታወሻ፡ ሰባኪው የዚህ ክፍል አውድ እንደ መግቢያ ልጠቀምበት ይገባል።

**መግቢያ፡**

የአንበጣ መንጋ እና ከፍተኛ ድርቅ ኢየሩሳሌምንና ይሁዳን ፈጽሞ አጥፍቷቸው ነበር። ነብዩም ይህንን በሀገርቱ ላይ የደረሰውን ከፍተኛ ጉዳት ‹‹[31]ታላቁና አስፈሪው የጌታ ቀን ›› ምልክት እንደሆነ ይናገር ነበር (ኢዮ 2፡31) በዚህ ችግር መካከል ሆኖ ሁሉም ሰው ንሰሓ ይገባ ዘንድ ይጣራል፡ ወጣት ሆነ ሽማግሌ (1፡2-3)፣ ሰካራሞች (1፡5)፣ ገበሬዎች (1፡11) እና ካህናት (1፡13) ሁሉንም ንሰሓ እንዲገቡ ይጠራቸዋል፡፡፡ የአንበጣ መንጋው የእግዚአብሔር ሠራዊት እንደሆነ፣ ታማኝ ያልሆነች እስራኤል በጌታ ቀን እንዴት እንደሚትቀጣ የሚያሳይ መሆንን ይናገራል፡፡ እግዚአብሔር በነብዩ በኩልበ የተሃድሶ ዘመን እንደሚመጣ እና እስራኤል ከኃጢአቷ ንሰሓ ብትገባ ከዚህ ቅጣት ውስጥ ባርኮት እንደሚፈስ የተስፋ ቃል ሰጥቷል፡፡

**ኃጢአት ሁል ጊዜበ ፍርድን ያመጣል**

- ሀ. የይሁዳ ሕዝቦች አምላካቸው ትተውታል/ክደውታል:
  1) ጌታቸው ይመለሱ ዘንድ ይጣራል (2:12, 13).
  2) አንቀላፍተዋል እንዲሁም መንፈሳዊ ሕይወታቸውን አልተበቁትን (1:3).
  3) ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይልቅ ለሥጋዊ ምቾታቸው ቅድሚያ ሰጥተዋል
     - ሀ) ‹‹ሰካራሞች›› እና ‹‹የወይን ጠጭዎች›› ተብለው ተጠርተዋል (1:3).
     - ለ) እርካታ ልገኝ የሚችለው ለአምላካቸው ካላቸው መሰጠት ነው
- ለ. እግዚአብሔር ይሁዳና እየሩሳሌል ለእርሱ ታማኝ ባለመሆናቸው ምክንያት ፍርድን በእነርሱ ላይ አምጥቷል
  1) ምድርቷን ፈጽሞ ያጠፋ ዘንድ የአንበጣ ሠራዊትን እግዚአብሔር ልኳል (2:11).
  2) የምግብ አቅራቦታቸው ሙሉ ለሙሉ ተቋርጧል (1:16, 17).
  3) ከጌታ ቤት ያገኙ የነበረው ደስታ እና ሓሴት ተወስዶባቸዋል (1:16).
  4) የውሃ አቅራቦታቸው ቀንሷል (1:20.)
- ሐ. ፍርድ ሁል ጊዜ ኃጢአትን ተከትሎ ይመጣል።
  1) የብሉይ ኪዳን የባርከትና የመርገም ሕግ (ዘዳ 11:26-28).
  2) የአዲስ ኪዳን የኃጢአትና የሞት ሕግ (ሮሜ 6:23).
- መ. የዘመናችን የኃጢአትና የፍርድ ምሳሌዎች:
  1) የቤተ ክርስቲያን ማህበረሰብ ውስጥ የመለኮታዊ ፍርድ ምልክት ምሳሌዎች
  2) በቤተ ክርስቲያንና በማህበረሰቡ ውስጥ የተለመዱ የኃጢአት ምሳሌዎች

(መጋቢው ግለሰቦችን በስም ሳይጠራ ወይም ሁኔታዎችን ሳይጠቅስ ኃጢአትን ማጋለጥ ይችላል)

3) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔር ክብር መጥፋት

ሠ. ለኃጢአት በተገቢው መንገድ መልስ ካልሰጠን ፍርድ የማይቀር ነገር ነው።

## 2. በጾም እና በጸሎት ሰዎችን ለንሰሓ መጥራት (2:12—17)

ሀ. በማህበረሰቡ የሚደረግ ንሰሓ:

1) በሙሉ ልባችሁ ወደ እኔ ተመለሱ (2:12, 13).

2) ንሰሓ እውነተኛ እና ከውስጥ መሆን አለበት እንጂ ለታይታ ውጫዊ መሆን የለበትም (2:13).

ሀ) ሰባኪው ውጫዊ ንሰሓ ምን እንደሚመስል ምሳሌ መስጠት አለበት እንዲሁም ይህ የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዲህ ያለውን ንሰሓ እንዴት እንደሚያወግዝ ማሳየት ይኖርበታል።

ለ. በማህበረሰቡ የሚደረግ ጸሎት

1) ወደ ጌታ ጩኹ (1:14).

2) በሙሉ ልባችሁ ወደ ጌታ ተመለሱ (1:12).

3) እግዚአብሔር ይታደጋችሁ ዘንድ ጥሩት (2:17).

4) በእግዚብሔር ፊት ሞገስ ለማግኘትና የእርሱ መገኘት በመካከላችሁ ይሆን ዘንድ ሰዎችን ለጸሎት አስተባብሩ

ሀ) ልዩ የሆነ ስብሰባ ጥሩ (1:14; 2:15,16)

ለ) ሽማግሌዎችንና በምድሪቷ ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ጥሩ (1:14).

ሐ) ሕጻናትንና አድስ ሙሽሮችን በዝህ ውስጥ አካቱ (2:16).

5) ጸሎት የእግዚብሔር ፊት የሚተፈልጉበት ይሁን እንጂ በሳዎች ፊት ሞገስ ለማግኘት የሚተሙክሩበት አይሆኑ (ማቴ 6:1-14).

ሐ. በማህበረሰቡ የሚደረግ ጾም

1) በጽዮን መለከትን ንፉ እንዲሁም ቅዱስ ጾምን አውጁ (1:14;2:15).

2) ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚያመለክተን የጋራ ጾምን እና ጸሎትን እንደሆነ አስታውሱ። ከዚህ በላይ በለ ቁጥር 4 ላይ የእምነት ማብረሰቡ በሙሉ እንድጾምና እንድጸልይ የተሰጠውን መመሪያ አስታውሱ።

3) በሙሉ ልብ የሚደረግ ጾም የንሰሓ እና የትህትና ምልክት ነው እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ ፈጽሞ መታመንን ያመለክታል (ማቴ 6:16-18)

## 3. ለእውነተኛ የንሰሓ ጸሎትና ጾም የእግዚአብሔር ምላሽ

ሀ. እግዚአብሔር ከቅጣት ወደ መባረክ ይመለሳል (2:13 እና 2 ዜና 7).

ለ. እግዚአብሔር ይቀናል እንዲሁም ሕዝቡን ይጠብቃል (2:18, 25).

ሐ. ወደ እርሱ ለተመለሱት እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ይሞላል (2:19, 26).

መ. እግዚአብሔር ለሕዘቡ ይገኛል (2:28-32; 3:21).

ሠ. 2:12 እና 3:28 እንዴት እንደምጀመር አስተውሉ፡

1) 2:12 - "አሁንም ቢሆን
2) 3:28 - "ከዚያም በኋላ"
3) በሙሉ ልባችን እግዚአብሔርን ከፈለግነው እንደሚገኝልን ቃል ግብቷል (ማቴ 5:6, 7; ሉቃ 11:5-13).

ረ. ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤ ቀን ይንን የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍል በመጠቀም በዚያን እለት የሆነው ነገር ኢዮ 2፡28-32 ላይ የተነበየው ነገር ፍጻሜ መሆኑን እንደገለጸ አስውሉ (ሐዋ 2:16-21 ተመልከቱ)

1) ነብዩ ኢዮኤል ለእኛ እውነተኛ ጸሎት ምላሽ እግዚአብሔር መንፈሱን እንደሚያፈስ ተናግሯል፡፡
2) ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህንን የኢዮኤል ትንብት የአዲስ ኪዳን ጴንጤቆስጤ ጋር አያይዞታል፡፡

## 4. በአፍሪካ ውስጥ ላለቸው የዘመናዊ ቤተ ክርስቲያን ያለው መልዕክት

ሀ. በአፍሪካ ውስጥ የሚትገኘው የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን መሠራዊ ዓላማዋ እና ተልዕኮዋ ግላዊ እና የጋራ የመንፈስ ቅዱስን መነቃቃት መለማመድ ነው (መንፈስ ቅዱስ በእኛ ለይ እድወርድ)

ለ. የአሁን ጊዜ አህጉራዊ መነሳሳታችን ቅድስና ንቅናቄ/ተሃድሶ ነው፡፡

ለ. መሠረታዊ ዓላማችን ልወጣ የሚገባው ከቅድስና ንቅናቄ/ተሃድሶ ውስጥ ነው፡፤

d. በአፍሪካ ውስጥ ትልቁ የሚያስፈልገን ነገር በቤተ ክርስቲያኖቻን ላይ መንፈስ ቅዱስ በሙላት ይወርድ ዘንድ ነው፡፡

### ማጠቃለያ:

ዛሬ በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ባሉ ቤተ ክርስቲያኖቻችን፣ ወጣት ሽማግሌ፣ ወንድ ሴት፤ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል እና አምልኮ የሚካፈሉ ሰዎች ስለራሳችን፣ ስለቤተ ክርስቲያናችን እና ስለማህበረሰባችን ንሰሓ ለመግባት በሚደረገው የጾም እና የጸሎት ፕሮግራሙ ላይ ይካፈሉ ዘንድ ይጠየቃሉ፤ በዚህም እግዚአብሔርን ከልባችን የሚንፈልግበት ጊዜ ይሆንልናል፡፡

የተወሰነ ጊዜ ስለ ጸሎትና ጾም የሚናስተምርበት ጊዜ ይኖረናል፡፡

ከዚያም ምእመኑን ለጸሎት የተዘጋጁ መሆኑን ጥይቁ፤ ስለ ራሳችሁ፣ ስለቤተሰባችሁ፣ ስለሀገራችሁ፣ ሰለአህጉራችሁ ለመጸለይ ተዘጋጅታችኋል ወይ?

የብሉ ኪዳን ኢዮኤልም ሆነ የአዲስ ኪዳኑ ጴጥሮስ በአንድ ድምጽ እንዲህ በማለት ያስተጋባሉ ‹‹እግዚአብሔርን በንሰሓ ልብ በጸሎትና በጾም ፈልጉት እርሱ መንፈስ ቅዱስን በእናንተ ላይ ዛሬ በአፍርካ እና በዓለም ሁሉ ላይ ያፈሳል፡፡

ለመጋቢዎች የተሰጠ ማስታወሻ፡ ምእመኖቻችሁን ቢያንስ ለሦስት ቀናት በጾም ጸሎት እንዲቆዩ ጠይቋቸው፡፡ የጾም ጸሎት ቀኑ መቼ እንደሚጀመር በመወሰን አስቀድማችሁ አስታውቋቸው፡፡

- መጾምና መጸለይ የሚችሉ ምንም ዓይነት ጤና ችግር የሌለባቸው ሰዎች ከውሃ በስተቀር ለሦስት ቀናት ምግብ ባይበሉ ይመረጣል፡፡
- የጤና ችግር ያለባቸው ግን በተለያየ መንገድ ልጾሙ ይችላሉ

*በቂስ ሃዊ ሹት ተዘጋጀ*

# ሕዝቤ እንዲህ ቢያደረግ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ 2ዜና** 7:11-16

2 ዜና 7:14

**መግቢያ:**

ይህ ስብከት በሕይወታችን በጣም የምንወዳቸውን ነገሮች እንደምንሰዋ ያሳየናል። የምንወደውን ነገር ለማግኘት ሁሉንም ነገር እድርጋለን። የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ ስጦታ ለማግኘትና በሕይወታችን እና በቤተ ክርስቲያናችን በእግዚአብሔር ቅባት ለመቀባት መስዋእትነት መክፍል አይጠበቅብንምን? ይህ ስብከት መንፈሳዊ መነቃቃት/ተሃድሶ በጣም እንደሚያስልገን ያሳየናል እንዲሁም በሕይወታችንና በዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ መነቃቃትተሃድሶ እንድከሰት የሚያስፈልጉ በእግዚአብሔር የተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎችንም ያሳየናል። ጸሎትና ጾም እግዚአብሔር በሕይወታችን፣ በቤተ ክርስቲያናችን፣ በማህበረሰባችን እና በአፍርካ ውስጥ እንድሠራ የሚያደርጉ ናቸው።

1. **መክፈቻ ምሳሌ**

   ሀ. በጣም ስለምትወዱት ነገር ምሳሌ ስጡ። ከዚህ በታች የተቀመጠው ምሳሌ ዓይነት የስብከቱን ዒላማ ለመምታት ይረዳል።

   *ምሳሌ፡*
   
   *የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ሳለሁ ላክሮስ የሚባል፣ በአሜርካ ውስጥ የሚኖሩ ሕንዶች የሚጫወቱትን ጫወታ እወድ ነበር። ይህ ጫወታ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ነበረው። በቡድኔ ውስጥ ጥሩ ተጫዋች የመሆን ፍላጎት ነበረኝ እንዲህ የምንገጥማቸውን ቡድኖች ሁሉ የማሸነፍ ፍላጎት ነበረኝ። በቡድኔ ውስጥ ካሉት ከየቤትኛውም ሰው በላይ ጠንክሬ ልምምድ አድርግ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ በመኖሪያ ቤታችን አከባቢ ጎል ሠርቼ እለማመመድ ነበር። ጓደኞቼ ማታ እንዲሁም በእረፈት ቀናት አንዳንድ ነገር አብረን እንድንሰራ ይጠይቁኛል እኔ ግን ግብዣቸው አልቀበለም ምክንያቱም ማሳለፍ የሚፈልገው በመለማመድ ነውና። ፍጹም ለመሆን ከፍተኛ ጥረት አድርግ ነበር። ውድድሮች ስኖሩ ለመመለማመድ በማለት ከትምህርት ገበታ እቀር ነበር በቡድኔ ውስጥ በጣም ጎበዝ ተጫዋች የመሆን ግቤን ለማሳካት ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጀሁ ነበርኩኝ። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለሁብ የነበረኝ ሕይወት ይህንን ይመስላል። ለዚህ እስፖርታዊ ጫወታ ከፍተኛ ፍቅር ነበረኝ።*

   *እግዚአብሔር ለዚህ እስፖርታዊ ጫወታ የነበረኝን ከፍተኛ ፍቅር ከጊዜ ወደ እያስታወሰ ለእግዚብሔር ነገርም እንዲህ ያለው ፍቅር ልኖረኝ እንደሚገባ ያሳስበኛል። በተለይም በሕይወቴ እና በቤተ ክርስቲያኔ ውስጥ መንፈሳዊ መነቃቃት/ተሃድሶን በከፍተኛ ፍቅር እንድፈልግ ይገፋፋኛል። በጣም ጎበዝ ተጫዋች ለመሆን የሚያስከፍለኝን ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጀት ነበርኩ። እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ጠየቀኝ በቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ መንፈሳዊ መነቃቃት/ተሃድሶ እንድከሰት እንዲሁም በልብህ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ እሳት እንድነድ አንተ ምን ታደርጋለህ?"*

   ሀ. ለቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት የቀረበ ጥያቄ:

   1) በሕይወታቸው ውስጥ ከፈተኛ መፍላጎት ያላቸው ለምንድ ነው እንዲሁም የሚፈልጉትን ለማግኘት መክፈል የሚፈልጉት ዋጋ ምን ያህል መሆኑን ጠይቃቸው።
   2) ‹‹በቤተ ክርስቲያንና በሕይወታችሁ ውስጥ መንፈሳዊ መነቃቃት/ ተሃድሶ ስመጣ ለመመልከት ምን ለማድረግ ትፈቅዳላችሁ?" በማለት ጠይቃቸው።
   3) 2 ዜና 7:14 እግዚአብሔር መነፈሳዊ መነቃቃት/ተሃድሶ የሚከሰትብትን መንገድ አሳይቶናል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚገኝበትን አውድ በጥንቃቄ እንመልከት።In

2. **የክፍሉ ታሪካዊ አውድ:**

ሀ. ንጉሥ ሰለሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ ገና መጨረሱ ነው፡፡

1) ለእግዚብሔር በምድር ላይ ማደሪያ ይሆን ዘንድ ቤተ መቅደሱን ሠራ

2) በመጨረሻም የቃል ኪዳኑ ታቦት በቤተ መቅዱሱ ውስጥ እንድቀመጥ ተደረገ

ሀ) የእግዚአብሔር መገኘት ሥፍራውን በጣም ሞልቶት ስለነበር ካህናቱ ወደ ቤተ መቅዱስ መግባት አልቻሉም ነበር (2ዜና 5:13-14).

ለ)ለዘመኗ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ የሚያስፈልጋት ነገር የእግዚአብሔር መገኘት ቤተ መቅደሳችን ይሞላ ዘንድ ነው (ቤተ ክርስቲያናችንንና የግል ሕይወታችንን)

ለ. በ2 ዜና 6 ላይ ሰለሞን በቤተ መቅደሱ ምረቃ ላይ ጸሎት ጸልዋል፡፡

1) የእስራኤል ሕዝቦች ሁል ጊዜ ኃጢአት እንደሚያድርጉ ሰለሞን አምኗል

2) ሰለሞን ወደ እግዚብሔር እንዲህ ስል ጸለየ፤ እስራኤላዊያን ወደ መቅደሱ መጥተው ከልባቸው ንሰሓ ቢገቡ እግዚአብሔር ይቅር ይላቸው ዘንድ ጸልይዋል፡፡

3) ሰለሞን ይህንን ጸሎት ጸልዪ ስጨርስ እሳት ከሰማይ መጥቶ የምቃጠለውን መስዋእት እና መስዋእቱን በላው እንዲሁም የእግዚብሔር ክብር ቤተ መቅደሱን ሞላው፡፡

4) ቀደምት ናዛሪኖች የእግዚአብሔር ክብር በሕይወታቸው እና በአምልኮአቸው ውስጥ ይታይ ዘንድ ይጸልዩ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያን እንደገና የእግዚብሔር እሳት በከፍተኛ ሁኔታ ያስፈልጋታል - በእኛ መካከል የእግዚአብሔር ክብር ስገለጥ መመልከት እንሻለን፡፡

ማስታወሻ፡ በዘመናችን ተሃድሶ እንደሚያስፈልግ ጥቂት ጊዜ ወስደህ አስደረዳ፡፡ በአፍርካ ውስጥ መንፈሳዊ ተሃድሶ እንድነሳ ሕዝቡ መጸለይ እንዳለበት አሳስብ፡፡

ሀ. እግዚብሔርም ለሰለሞን ተገለጠለትና የሕዝቡን ኃጢአት ይቅር እንደሚል እንዲሁም በምድርቱ ላይ ተሃድሶን እንደሚያመጣ ቃል ገባለት፡፡ ይህ ነገር በዘመናችንም የሚያስፈልገን በመሆኑ እግዚአብሔር ለሰለሞን የሰጠውን ምለሽ በጥንቃቄ እንመልከተው፡፡

3. **የተሃድሶ የተስፋ ቃል:**

ሀ. የተሃድሶ ቀመር፡ እግዚብሔር ለሰለሞን ማታ ላይ በተገለጠለት ጊዜ እንዲህ አለው ‹‹[14]**በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ እስራኤላውያን ራሳቸውን አዋርደው ከሚያደርጉት ክፉ ነገር በመራቅ ተጸጽተውና ንስሓ ገብተው ወደ እኔ ቢጸልዩ በሰማይ ሆኜ እሰማቸዋለሁ፤ ኃጢአታቸውን ይቅር እልላቸዋለሁ፤ ምድራቸውም እንደገና ፍሬያማ እንድትሆን አደርጋለሁ”**

1) ይህ የተስፋ ቃል የተሰጠው ለእስራኤል ነው፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ፡፡ ነገር ግን በትክክለኛው መንገድ የእግዚአብሔር ሕዝብ ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ በእርሱ ስም የተጠሩት ክርስቲኖች ናቸው፡፡ ይህ የተስፋ ቃል ለእኛ ነው፡፡

2) ‹‹ቢ . . .›› የተስፋ ቃሉ መጀመሪያ

**"[14]በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ እስራኤላውያን ራሳቸውን አዋርደው ከሚያደርጉት ክፉ ነገር በመራቅ ተጸጽተውና ንስሓ ገብተው ወደ እኔ ቢጸልዩ በሰማይ ሆኜ እሰማቸዋለሁ፤ ኃጢአታቸውን ይቅር እልላቸዋለሁ፤ ምድራቸውም እንደገና ፍሬያማ እንድትሆን አደርጋለሁ"**

ለ. የእግዚብሔር ድርሻ - የተሃድሶ የተስፋ ቃል.

1) ጸሎታችንን ይሰማል

2) ኃጢአታችን ይቅር ይላል

3) ምድራችንን ይፈውሳል (ማህበረሰባችንን፣ ሀገራችንን፣ ቤተ ክርስቲያናችንን).

4) ይህ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ነው- እርሱ ያስቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ካሟላን ሕይወታችን እና ቤተ ክርስቲያናችንን እንደገና ያድሳል።

5) እኛ ተሃድሶ እንድመጣ እየተበቅ ነው ነገር ግን ተሃድሶ እኛን እየጠበቀን ነው። እግዚብሔር ያስቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ስናሟላ ተሃድሶ ይመጣል።

**[14]በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ እስራኤላውያን ራሳቸውን አዋርደው ከሚያደርጉት ክፉ ነገር በመራቅ ተጸጽተውና ንስሓ ገብተው ወደ እኔ ቢጸልዩ በሰማይ ሆኜ እሰማቸዋለሁ፤ ኃጢአታቸውን ይቅር እልላቸዋለሁ፤ ምድራቸውም እንደገና ፍሬያማ እንድትሆን አደርጋለሁ**

c. የእኛ ድርሻ - የተሃድሶ ቅድመ ሁኔታ:

1) ራስን በማዋረድ መጸለይና የእግዚብሔርን ፊት መፈለግ

ሀ. ራስን ማዋረድ ማለት፡ በእርሱ ላይ መደገፍ፣ ራስን ዝቅ ማድረግ፣ ማዋረድ ማለት ነው።

ለ. በመጀመሪያ ይህ የልብ ሁኔታ ሲሆን በእግዚአብሔር ፊት እኛ ምንም አለመሆናችንን መገንዘብ ነው፤ በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም በሆነ መልኩ መደገፍ። የእግዚብሔርን ፊት መፈለገ በእርሱ ላይ ፈጽሞ መደገፍን ያመለክታል።

ሐ. የብሉይ ኪዳን ሰዎች ጸሎትንና ጾምን ራሳቸውን በእግዚብሔር ፊት የሚያዋርድበትና ከእርሱ የሚፈልጉትን ነገር የሚጠይቁበት መንገድ አድርገው ይመለከቱታል። (መዝ 35:13 እና ዳን 9:3 ይመልከቱ).

መ. የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ጸሎትንና ጾምን የእግዚአብሔር ፈቃድ ለማወቅ እና በሕይወታቸው የእርሱን ባርኮት ለመቀበል ተለማምደውታል። (ሐዋ 14:23 ተመልከት).

ሀ) ያለምንም ምግብ ለረጅም ጊዜ ስንቆይ ለእግዚብሔር የሚናስተላልፈው መልዕክት ከእኛ ምኞት ይለቅነ እርሱ እንደሚንፈልገው ነው ነገር ግን ከንሰሓ ውጭ የሚደረግ ጾም ግን ትርጉም አልባ ነው።

2) ንሰሓ: ከጥፋት መንገዳችን ልንመለስ ይገባል (እግዚብሔር ከሚያሳዝኑ ነገሮች)

ሀ) በማህበረሰባችሁ ወይም በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚደረጉ ነገር ግን እግዚብሄር የማያስከብሩ ነገሮችን በማንሳት ለአጭር ደቂቃ ተናገሩ፤ ከዚያም ሰዎች እንዲህ ያለውን ነገር እንዲያቆሙ ንገራቸው።

ለ) እግዚአብሔር የሚያስደስተውና እጆቹን የሚያንቀሳቅሱት እውነተና ጾሞች ከኃጢአት መንገዳቸው በተመለሱ ሰዎች የሚጸለይ ጸሎት ነው።.

**4. ምሳሌ - ቻርሌስ ፊኒ - በ19ኛ ክፍለ ዘመን ይኖር የነበረ አሜሪካዊ ወንጌላዊ ሲሆን በአሜሪካ ውስጥ ሁለተኛው መነቃቃት በተነሳ ጊዜ እግዚብሔር በከፍተኛ ሁኔታ ተጠቅሞበታል።**

ሀ. ፊኒ በታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ይሰብክ ነበር

1) እርሱ ይሰብክባቸው በነበረባቸው በታላላቅ የተሃድሶ ስብሰባዎች ውስጥ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እየተወቀሱ ኃጢአታቸውን ይናዘዙ ነበር፣ ንሰሓ የማይገቡና የእግዚአብሔር ፊት የማይፈልጉ ከሆነ ግን ወዲያውኑ ይሞቱ ነበር።

2) አንድ ጊዜ ማታ ላይ የተሃድሶ ስብሰባውን እያደረገ ሳለ አንድ ፋብሪካ ለመጎብኘት ወሰነ። የፋብሪካው ተቆጣጣሪ ሰራተኞቹ ስራ ላይ እያሉ እርሱ ለመጎብኘት ወደ ክፍሉ ገባ። በአንድ ሴት ለቅሶ የተጀመረ ፋብሪካው ስራውን እስክያቆም ድረስ እያንዳንዱ ሰራተኛ እያለቀሰ ከኃጢአቱ ንሰሓ ይገባ ጀመረ። ፊኒ ምንም ቃል አልተነፈሰም ነበር። የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በእርሱ ላይ ስለነበር እርሱ በገባበት ክፍል ሁሉ ውስጥ የእግዚብሔር መገኘት ሰዎች ይሰማቸው ነበር። ተቆታጣሪውም ፊኒን ለሰዎች ይናገር ዘንድ ለመነው።

ፊኒ ስለ ክርስቶስ ነገራቸው፣ ኃጢአታቸውንም ይናዘዙ እና ክርስቲስን ይቀበሉት ዘንድ አበረታታቸው። በዚያ ፋብሪካ ውስይ ይሠሩ የነበሩ ሰዎች ሁሉ በዚያ እለት ጌታን ተቀበሉ።

ለ. የፊኒ ስኬት ምስጥር፡

1) ቻርለስ ፊኒ እንዲህ በማለት ስለ ራሱ ታሪክ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ይገልጻል። አባት ናሽ የተባሉ ሰው የተሃድሶ ስብሰባው ይደረጋል ከተባለበት ሁለት ሰምንታት በፊት ስብሰባው ወደ ምደረግበት ስፍራ ይሄዳሉ። በከተማው ውስጥ አንድ ወይም ሁለት ጥሩ ክርስቲኖችን ይፈልግና ይጸልያል። ናሽ እና የአከባቢው ክርስቲያኖች ምግብ ሳይበለው በጌታ ፊት በመቅረብ እግዚአብሔር ፊኒን እንድቀባው እና በከተማቸው ውስጥ ተሃድሶ ይሆን ዘንድ ይጸልያሉ። ፊኒ እንዲህ ይላል፤ አባት ናሽ ቀድመውት በሄዱበት ስፍራ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚሠራ እና ሰዎችን እንደሚወቅስ ይናገራል። ነገር ግን ናሽ ከእርሱ ፊት ቅድሞ ካልሄድ ስብከቱ ምንም ጉልበት እንደሌለው፣ ምንም በሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ለውጥ እንደማያመጣ ይነገራል።

2) እግዚብሔር በጾም ጸሎት ለሥራ ይነሳሳል እንዲሁም ከፊኒ ስብከት ይልቅ የናሽ ጾምና ጸለት እግዚአብሔርን ለሥራ ያነሳሳል።

**ማጠቃለያ፡ የመሰጠት ጥሪ**

መጋቢው ምእመናኑን የእግዚአብሔር ክብር ምን ያህል እንደሚፈልጉ ይጠይቃቸዋል። የቅድስና ተሃድሶ እንድመጣ ምእመኑ በጠቅላል የጾም እና የጸሎት ጊዜ እንድኖረው መገፋፋት። :

- በሕይወታቸው
- በቤተሰባቸው
- በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው
- በማህበረሰባቸው ውስጥ
- በአፍርካ አህጉር ውስጥ በሚገኙ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ

*By Rev Howie Shute*